# ስለ ኩፍኝ 5 እውነታዎች

## እውነታ 1 የኩፍኝ በሽታ በቫይረስ አማካኝነት የሚከሰት እጅግ ተላላፊ የሆነ በሽታ ነው።

ኩፍኝ፣ የታመመው ሰው **በሚያስልበት ወይም በሚያስነጥስበት ወቅት ወደ አየር ውስጥ ይሰራጫል።** ቫይረሱ፣ ኩፍኝ ያለበት ግለሰብ ከአካባቢው ከሄደ በኋላ እንኳ፣ ለሁለት ሰዓታት ያክል በአየር ውስጥ መቆየት ይችላል።

በኩፍኝ በተጠቃ ሰው አቅራብያ ከነበሩ **አስር ሰዎች ውስጥ ዘጠኙ ፣** ካልተከተቡ **በቀር** በቫይረሱ የሚጠቁ ይሆናሉ።

## እውነታ 2 ኩፍኝ እጅግ አደገኛ ሊሆን ይችላል

ኩፍኝ **ለጨቅላ ሕፃናት እና ለልጆች ፣እጅግ አደገኛ** ሊሆን ይችላል።

አምስት በኩፍኝ ከሚጠቁ ሰዎች መካከል አንዱ **ሆስፒታል ይተኛል ።**

ኩፍኝ ለ **ሳንባ ምች** (አደገኛ የሆነ የሳንባ ኢንፌክሽን)፣ ለአንጎል ጉዳት፣ ለመስማት ችግር እና ለሞት ሊዳርግ ይችላል።

**የአንጎል ሕብረ ህዋሳት ብግነት (Encephalitis)** በኩፍኝ ከሚጠቁ 1,000 ሕፃናት መካከል አንዱ፣ encephalitis (የአንጎል እብጠት) ያጋጥመዋል። ይህም ሕፃኑ መስማት እንዳይችል እና የአስተውሎት እክል እንዲገጥመው ሊያደርግ የሚችል ነው።

**ሞት** በኩፍኝ ከሚጠቁ 1,000 ሕፃናት መካከል፣ ከ 1 እስከ 3 የሚሆኑት በመተንፈሻ አካላት እና የኒውሮሎጂ ውስብስብ ችግሮች ምክንያት ህይወታቸውን ሊያጡ ይችላሉ።

## እውነታ 3 የኩፍኝ ምልክቶች

- **ከፍተኛ ትኩሳ**
- **ሳል**
- **ንፍጥ**
- **የዓይን መቅላት/ወይም ከዓይን እንባ መፍሰስ**
- **ሽፍታ**

## እውነታ 4 ሁነኛው የመከላከያ መንገዱ ክትባት ነው

- ኩፍኝን ለመከላከል ጥሩው መንገድ፣ **MMR (measles-mumps-rubella) ክትባት ነው።**
- የ MMR ክትባት **ሁለት መጠን (dose)** ፣ የኩፍኝ ኢንፌክሽንን በመከላከል ረገድ **97%** ውጤታማ ነው።




### ሕፃናት፣ የ MMR ክትባትን ሁለት መጠን (dose) እንዲወስዱ ይመከራል።

- **የመጀመሪያው መጠን (dose)** ከ **12 እስከ 15 ወር ባለው እድሜ ውስጥ**
- **ሁለተኛው መጠን (dose)** ከ **4 እስከ 6 ዓመት** ባለው እድሜ ውስጥ (ትምህርት ቤት ከመግባት በፊት)

## እውነታ 5 MMR ክትባት፣ የሕይወት ዘመን ጥበቃ ይሰጣል




MMR ክትባትን ከተከተቡ ሰዎች ውስጥ አብዛኞቹ፣ **እድሜ ልካቸውን** በቫይረሱ አይጠቁም።

ክትባትን መውሰድ፣ የበሽታዎችን ስርጭት በመከላከል **ማህበረሰብዎን ለመጠበቅ** ይረዳል።

የልጅዎን **የ MMR ክትትብ ሁኔታ** ለማወቅ፣ https://www.vdh.virginia.gov/immunization/request-immunization-record/ ይጎብኙ።
ለልጅዎ **ክትባት ማግኘት ላይ** ላይ እገዛ ከፈለጉ፣ https://www.vdh.virginia.gov/immunization/provider-locator/ ይጎብኙ።
ስለ ኩፍኝ **ተጨማሪ ነገር ማወቅ ከፈለጉ** ፣ vdh.virginia.gov/measles ይጎብኙ።

VDH VIRGINIA DEPARTMENT OF HEALTH